# በእነ አቶ ሀይሉ ሻውል ጉዳይ የፍርድ ቤቱ ብይን ላይ የቀረበ አስተያየት

በሀራችን የተካሄደውን የግንቦት 7/1997 ዓም ምርጫ ተከትሎ ተቃዋሚዎች ባነሳሱትና በመሩት አመፅ መነሻነት በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን አደጋ ላይ ለመጣል ያነጣጠሩ ሁለት የአመፅ እንቅስቃሴዎች ተከስተዋል፡፡ በአመፆቹ ምክንያት በህግ አስከባሪዎች ላይ የህይወትና የአካል ጉዳት ደርሷል፣ በግለሰቦች ላይ ጥቃት ተሰንዝሯል፣ በህግ ማስከበር ሂደትና አመፁን በማስቆም ጥረት የግለሰቦች አካልና ህይወት ተጎድቷል፣ የግልም ሆነ የመንግስት ስራ እንዲቆም ተገዷል፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ተቋርጧል፣ በህዝብና በመንግስት ንብረት ላይ ውድመት ተከስቷል፡፡

እነዚህ አመፆች የተነሱት ተከሳሾቹ በየወቅቱ ለደጋፊዎቻቸው በተለያዩ ሚድያዎችና መንገዶች በሚያደርጉት ቅስቀሳ አማካኝነት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በስርአቱ ውስጥ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ላማከሄድ እንደማይቻል፣ ምርጫውን ገዢው ፓርቲ እንደሚያጭበረብር፣ የተጭበረበረ ምርጫ ደግሞ በሰርአቱ ለማረም እንደማይቻል፣ ነፃና ገለልተኛ የፍትህ ተቋማት እንደሌሉ፣ እነርሱም በነዚህ ቅሬታቸውን ለመፍታት እንደማይጠቀሙ፣ ይልቁን በስም ሽፋፍነው በማቅረብ ሊወሰድ ይገባል የሚሉትና የሚያበረታቱት ህጋዊና ሰላማዊ አመፅ ደጋፊያቸው የራሱን መብት እንዲያስከብር ጥሪ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ መብትህን አስከብር በሚል ሽፋን ህጉን በእጁ ወስዶ አመፅና ሁከት እንዲነሳ በዚህም ስርአቱን አስገድዶ ስልጣን ለማስለቀቅ የታለመ ተግባር ሲያከናውኑ ቆይተዋል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለአመፁና ለህገወጥ ድርጊቶቹ የህግ አስከባሪ አባላት ተግባራቸውንና ግዴታቸውን እንዳይወጡ በዝምታ እንዲያልፉ ሲቀሰቅሱ ቆይተዋል፡፡ በመከላከያ ሀይላችን ንብረትና ተቋማት ላይም ጥቃት ተሰንዝሯል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አንድ ብሔረሰብንና የፖለቲካ ቡድንን መሰረት ያደረገ ማግለልና ጥቃት ማድረስ እንዲፈፀም ሁኔታዎችን ሲየመቻቹ ቆይተዋል፡፡

የመንግስት ስልጣን በአንድ ብሔረሰብ እንደተያዘ በማቅረብና አለ በማለት የሚቀሰቅሱትን በደል የሚፈፅመው ገዢው ፓርቲ እንደሆነ በማቅረብ ደጋፊያቸው በነዚህ አባላት ላይ ጥቃት እንዲፈፅም አድርገዋል፡፡

ተከሳሾቹ ይህን ህገወጥ አላማቸውን ለማስፈፀም ከጠላት መንግስት ጋር ትብብር አድርገዋል፡፡ የሀገራችን የመንግስት ስርአት በትጥቅ ለማፍረስ በኤርትራ መንግስት ከሚደገፈውና ከሚሰማራው የአርበኞች ግንባር ጋር ግንኙነት ፈጥረዋል፡፡

በተመሳሳይም በራሳቸው በህቡዕ ስርአቱን የማፍረስ እንቅስቃሴያቸውን ለመደገፍ በተወሰኑ አካባቢ ያሉ ደጋፊዎቻቸውን ትጥቅ አንስተው የመንግስት ስርአቱን ለመጣል እንዲንቀሳቀሱ ሲያደራጁና ሲያስተባብሩ ነበር፡፡

ይህን ሁሉ በህገ መንግስታችንና በስርአታችን ላይ ያነጣጠረ ወንጀል በተገቢው የህግ ማስከበር ሂደት እንዲከሽፍ ከተደረገ በኋላ በወንጀሉ የተሳተፉትንና በተለይ ይህን የወል የወንጀል አድማ አላማ በመጠንሰስና በመምራት የተሳተፉት ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚሁም መሰረት በእነ አቶ ሀይሉ ሻውል (111 ሰዎች) ላይ በፌደራል ዐቃቢ ህግ ታህሳስ 26/1998 ዓ.ም በቀረበባቸው 6 ክሶች 1ኛ ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በህገወጥ መንገድ የማፍረስ ሙከራ ወንጀል፣ 2ኛ በህገ መንግስቱ ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባሩን እንዳያከናውን የማሰናከል የወንጀል ድርጊት መፈፀም፣ 3ኛ በመንግስት ላይ የትጥቅ አመፅ የማነሳሳት የማደራጀትና የመምራት ወንጀል መፈፀም፣ 4ኛ የሀገር መከላከያ ሀይልን የመጉዳት ወንጀል መፈፀም፣ 5ኛ በሀገር ላይ ከፍ ያለ ክዳት ወንጀል መፈፀም፣ 6ኛ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሙከራ ክሶች መሆኑ ይታወሳል፡፡

ፍርድ ቤቱ በሀገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርአት ህግ መሰረት በግልፅ ችሎት ታዛቢዎች ጭምር ባሉበት ክሱን መስማት ቀጥሏል፡፡ በዚህ በክስ የመስማቱ ሂደት ፍርድ ቤቱ በተከሳሾቹ ላይ የቀረበውን ክስ ከነማስረጃው እንዲደርሳቸው አድርጎ ካነበበላቸው በኋላ እንደተረዱት በማረጋገጥ ይህን ከባድ የወንጀል ክስ ሂደት

በጠበቃ ወይም በምን አይነት ሁኔታ ለመከራከር እንደሚሹ ተጠይቀው የተወሰኑት በራሳቸው ጠበቃዎች አማካኝነት እንደሚከራከሩ ሲገልፁ አብዛኞቹ አንከራከርም ቢሉም በህጉ መሰረት መንግስት ጠበቃ ሊያቆመላቸው እንደሚችል ቢነገራቸውም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ወደ ቀጣዩ ስርአት ተሻግሯል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹ ክሱን ይቃወሙ እንደሆነና እምነት ክህደት ቃላቸውን ጠይቋቸዋል፡፡ የተወሰኑት ተከሳሾች ክሱን ሲክዱ አብዛኞቹ በዝምታ ገልፀዋል፡፡ በስነ ስርአት ህጉ መሰረት ዝምታም እንደ መካድ መልስ የሚቆጠር በመሆኑ ድርጊቱን እንካዱ መገመት ዐቃቢ ህግ ክሱን እንዲያስረዳ ማስረጃዎቹን እንዲያቀርብ አዟል፡፡ ዐቃቢ ህግም ብዛት ያላቸው የቪድዮ፣ የኦድዮ፣ የሰነድና የሰው ማስረጃዎችን ለፍርድ ቤቱ አቀርቦ በግልፅ ችሎት አሰምቷል፡፡ በዚህ የማስረጃ መስማት ሂደት ተከሳሾቹ የማስረጃ ተቀባይነትን አስመልክቶ ተቃውሞ ቅርበዋል፣ መስቀለኛ ጥያቄዎችንም በመጠየቅ ክርክር አካሂደዋል፡፡

የዐቃቢ ህግን ማስረጃ የመስማቱ ሂደት እንዳበቃም ፍርድ ቤቱ የቀረቡትን ማስረጃዎች ከህጉ ጋር አገናዝቦ በክሱ የተመለከተውን ድርጊት ለመፈፀሙ ያስረዳ እንደሆነ ለመመርመር ቀጠሮ በመስጠት ጉዳዩን አጥንቶታል፡፡ ከመጋቢት 21/1999 ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ለስድስት ቀን ብይን በመስጠት ሚያዝያ 1/1999 ዓ.ም ብዩን አጠናቆ ሰጥቷል፡፡ በብይኑ ላይ የሚታዩ አሉታዊና አዎንታዊ ሁኔታዎች እንደሚከተለው በትችት መልክ ይቀርባሉ፡፡

ብይኑ ዝርዝርና በስነ ስርአት ህጉ መሰረት ምክንያት የሚገልፅ ሀተታ ያለው በመሆኑ ተገቢ ይዘት አለው፡፡ የቀረቡት ማስረጃዎች ስፋትና ጥልቀት ቢኖራቸውም በተቻለው መጠን አብዛኛውን ለመመርመና ለመተቸት የቻለ ነው፡፡

የዚህ ብይን ሌላው አዎንታዊ ጎን በአንደኛው ክስ ማለትም ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በህገወጥ መንገድ የማፍረስ ሙከራ ወንጀል ክስ ላይ በሰጠው ብይን መሰረት የሰኔ 1/1997 እና የጥቅምት 1998 አመፅ ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን በህገወጥ መንገድ የማፍረስ ሙከራ ድርጊት መሆኑን፣ ቅንጅትና በቅንጅት ዙሪያ የተሰባሰቡት ተከሳሾች ይህን ወንጀል በመቀስቀሳቸውና

መነሻ ምክንያት በመሆናቸው ተጠያቂ እንደሆኑ አረጋግጧል፡፡ ይህ የሀገራችን ዴሞክራሲ ከፍተኛ ድል ሲሆን ከእንግዲህ ወዲህ ህገ መንግስቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተመሳሳይ የጥፋት፣ የአመፅና የወንጀል ስራ እንዳይሰራ አስተማሪ የሆነ ብይን ነው፡፡ በተለይም በምርጫ ሰበብ ተከሳሾቹ የተከተሉትን የምርጫና የፍትህ ተቋማት በማጥላላትና ደጋፊን በመቀስቀስ፣ እንዲሁም በህጋዊና ሰላማዊ ትግል ሽፋን በህገ መንግስቱ ከተመለከተው የቅሬታ መፍቻ ስርአት (ከህግ የበላይነት) ውጪ ማንም ሊሄድ እንደማይችል አስተማሪ ብይን ነው፡፡

ይህ የፍርድ ሂደት የህግ የበላይነተን ያሰፈነ በዚሁም ረገድ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ በሀገራችን የጀመርነው የዴሞክራሲና የልማት ግንባታ የህግ የበላይነትን ከማክበርና ከማስከበር ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ስርአታችን ከዚህ ቀደም ባሉ የተለያዩ አጋጣሚዎች የህግ የበላይነት ያረጋገጠ መሆኑ በተለያዩ የፍርድ ሂደቶች የታየ ቢሆንም፣ በዚህ በያዝነው ጉዳይ በህገወጥ መንገድ ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ለማፍረስ ሙከራ ያደረጉት የግለሰቦችና የቡድኖች አካሄድ በህግ አስከባሪዎች ተገትቶ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ሂደት እንዲታይ መደረጉ የህግ የበላይነትን በሀገራችን ከማስፈንና ከማረጋገጥ አንፃር ከፍተኛ ሚና ያለው የፍርድ ሂደት መሆኑ አሌ የማይባል ሀቅ ነው፡፡

የህግ የበላይነት ማናቸውም ሰው በህጉ መሰረት መገዛት እንዳለበትና የፍርድ ሂደት ጉዳይ በህግ ስርአትና በህግ ብቻ መሰረት ማለቅ እንዳለበት የግድ የሚል ነው፣ እንዲሁም ማንም ሰው ይሁን ቡድን ከህግ በላይ ሊሆን እንደማይችል የፍትሐብሔርም ሆነ የወንጀል ጉዳይ በህግ መሰረት እንደሚዳኝ የሚያረጋግጥ ሂደት ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ ተከሳሾቹ እነ ሀይሉ ሻውል ከመከሰሳቸው በፊት በሀገራችን ነፃ ፍርድ ቤት የለም፣ የምርጫ ቅሬታችንን ፍርድ ቤት አንወስድም፣ ከተከሰሱም

በኋላ በዚህ ፍርድ ቤት አንከራከርም በማለት እውቅና እና ክብርን ለፍርድ ቤቶቻችን ለመንፈግ የሞከሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ይህው ፍርድ ቤት ግን፣ ጉዳያቸውን በህጉ መሰረት መርምሮ ለማንኛውም ዜጋ የተከበሩ መብቶችና ነፃነቶችን ለተከሳሾቹም ጠብቆና አክብሮ፣ ፍርድ ቤቱ ብይን ሰጥተዋል፡፡ የዘር ማጥፋት ሙከራና ወንጀል ክስንና ከፍ ያለ የሀገር ክህደት ወንጀል ክሶች ውድቅ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በትጥቅ ትግል በማደራጀት ክስ የቅንጅት አመራር የነበሩትን አብዛኞቹን ተከሳሾች፣ በውጭ ሀገር ያሉ ተከሳሾችን እና የጋዜጣ ም/አዘጋጆችን ከነ ባለቤቶቻቸው በነፃ አሰናብቷል፡፡ ይህ የፍርድ ሂደት በሀገራችን የተጀመረውን የዴሞክራሲና የልማት ግንባታ ሂደት ለመጠበቅና ለመገንባት የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ያለው መሆኑን ያረጋገጠ ሂደት ነው፡፡

የፍርድ ሂደቱ ሌላው ያረጋገጠው ጉዳይ በሀገራችን የዳኝነት ነፃነት የተከበረ መሆኑን ነው፡፡ እንደሚታወቀው የዳኝነት ነፃነ ዳኞች ካለ ማንኛውም ተፅእኖ ጉዳዮችን በህጉ መሰረት ብቻ መወሰን የሚችሉበትን ሁኔታ የሚጠይቅ ነው፡፡ እንደ የህግ የበላይነት ሁሉ የዳኝነት ነፃነት ህገ መንግስታችንና ስርአቱ የተቋቋመበትና የሚመረኮዝበት ምሰሶ ነው፡፡ የመሰረት ምሰሶዎች አንዱ ነው፡፡ በያዝነውም ጉዳይ ዳኞች በብይናቸው እንዳሰፈሩት የዐቃቢ ህግን ማሰረጃ ከህጉ ጋር በማገናዘብ የተረዱትን በመተንተን በይነዋል፡፡ በህግና በራሳቸው ህሊና መሰረት የመሰላቸው ይህ ብይን፤ ዐቃቤ ህግ ካቀረባቸው ክሶች የዘር ማጥፋት ሙከራ ወንጀል ክስ እና ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል ክስን ውድቅ ያደረገ ብይን ነው፡፡ ይህ ብይን በርካታ ተከሳሾች ላይ ዐቃቤ ህግ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች በተከሰሱበት ወንጀል ተከላከሉ ሊያስብሉ የማይችሉ ናቸው በማለት በነፃ ያሰናበተ ብይን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው ምንም እንኳን በዐቃቤ ህግ በኩል ብይኑ ቅሬታ ሊያሳድር የሚችል መሆኑ ቢገመትም ዐቃቤ ህግ ቅሬታ ካለው በህግ መሰረት ቅሬታውን በይግባኝ መልክ ለሚመለከተው

የበላይ ፍርድ ቤት ከማቅረብ ባሻገር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ብይን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

በዚህ የፍርድ ሂደት ምንም እንኳን በመንግስት በኩል በዳኝነት ነፃነት ላይ የተደረገ ተፅእኖ የሌለ ቢሆንም ወይም ለመኖሩ አንዳች ተጨባጭ ጠቋሚ ባይኖርም ከመንግስት ውጭ ግን በአደባባይ በፍርድ ሂደቱ ላይ ከፍተኛ የስነ ልቦናዊና ቁሳዊ ተፅእኖ ሲደረግ ተስተውሏል፡፡ የተለያዩ ታዋቂ ነን የሚሉ ሰዎች እና አንዳንድ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች የፍርድ ሂደቱ ተቋርጦ የህግ የበላይነትን ማረጋገጡ ቀርቶ በምህረት ወይም በይቅርታ ተከሳሾቹ እንዲለቀቁ የየራሳቸውን ከንቱ ሩጫ በየፍርድ ቤቱ፣ በየመስሪያ ቤቱ እንዲሁም በተለያዩ አጋጣሚ መድረኮች ሲያደርጉ ታይተዋል፡፡ አሁንም እነዚህ ሰዎች በዳኝነቱና በፍርድ ቤት ነፃነት ላይ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ጫና የማድረግ እንቅስቃሴያቸው አላባራም፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ተከሳሾች የተከሰሱባቸው ወንጀሎች ከባድ ወንጀሎች ከመሆናቸውም በላይ በተለይ የዘር ማጥፋት የሚያካትት በመሆኑ በሀገራችን ህግም ሆነ በአለማቀፍ ህግ ይቅርታም ሆነ ምህረት የማይሰጥበት ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዳኞች ነፃነት ላይ በተለያዩ አቅጣጫዎች እየተደረጉ ያሉት ጫናዎች ምናልባትም በተጠቀሱት ተከሳሾች ላይ ከቀረቡት ክሶች መካከል የተካተተው የዘር ማጥፋት ወንጀል ክስ ላይ ፍርድ ቤቱ የጥፋተኛነት ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ በወንጀሉ ይቅርታም ሆነ ምህረት ሊሰጥ የማይችልበት መሆኑን መነሻ ያደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የህግ የበላይነትና የዳኝነት ነፃነት ማክበርና ማስከበር የማናቸውም የዴሞክራሲ ስርአት ያላቸው ሀገሮች ቁልፍ ተግባር በመሆኑ በፍርድ ሂደት በተያዘ ጉዳይ ላይ እየተደረገ ያለው ጫና ተቀባይነትም ሆነ አንዳችም ፋይዳ የማይኖረው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡ በዚህ ጉዳይ የህግ የበላይነትን ወደ ጎን በመተው

መንግስትም ቢሆን ይቅርታ ወይም ምህረት የማድረግ መብትም ሆነ ስልጣን የለውም፡፡

ብይኑ የህግ የበላይነትንና የዳኝነት ነፃነትን ከማረጋገጥ አንፃር ሲታይ ከፍ ያለ ጠንካራና በጎ ጎኖች ያሉት ቢሆንም በህግ እና በማስረጃ ምዘና አንፃር ሲታይ ግን ሊተቹ የሚገባቸው ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ጎኖችም አሉት፡፡
ብይኑ በዋነኛነት ዐቃቤ ህግ ክሱን መሰረት ያደረገበትን የዐድማ ትስስር (Conspiracy) ያልተቀበለ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ህግን የአድማ ትስስር ጥያቄ ሳይቀበል ተከሳሾቹን በቡድንና በነጠላ በመለየት ብይኑን ሰጥቷል፡፡

አድማ (Conspiracy) ሰዎች አንድን የወንጀል አላማ ለማሳካት ስምምነት አድርገው ይህንኑ ወንጀል ሲፈፅሙ ወይም ሲሞክሩ የሚነሳ የወንጀል ተሳትፎን የሚያመለክት ሀሳብ ነው፡፡ በአድማ ውስጥ ለመሳተፍ የሚያስፈልገው የወንጀል አላማውን አውቆ መቀበል ብቻ ነው፡፡ አድመኞቹ በሙሉ በአካልም ሆነ በቦታ የሚተዋወቁ መሆን የለባቸውም፡፡ ስምምነታቸውም በፊርማና በግለፅ የሚቀርብ አይደለም፡፡ ይልቁንም በድርጊትና በአካባቢያዊ ሁኔታ የጋራ አላማ እንዳላቸው ማሳየት በቂ ነው፡፡ ይህ ወንጀል ለመፈፀም ያለ ስምምነት ብቻ በተለያዩ ሀገሮች የሚያስቀጣ ነው፡፡ በሀገራችንም ቢሆን ለከባድ ወንጀሎች መፈፀማቸው ሳይጠበቅ ለመፈፀም ስምምነት ካለ የሚቀጡ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ በያዝነው ጉዳይ ግን ዐቃቤ ህግ ያቀረበው በወንጀል የመፈፀም ስምምነት እና የተፈፀመውን ወንጀል ጭምር ነው፡፡ የአድማ ተሳታፊ ሰው የግድ ሁሉንም ተግባር መፈፀም አይኖርበትም፡፡ ከወንጀል ፈፃሚዎቹ ብዛት አንፃር ይህ የወንጀል መፈፀም የጋራ ስመምነት ያላቸው ሰዎች ከአደገኛነታቸው አንፃር በሙሉ ለመቅጣት የገራችንም ህግ ቢሆን ይፈቅዳል፡፡ ፍርድ ቤቱ ግን ሙሉ ለሙሉ ይህን የወል ወንጀል የመፈፀም ስምምነት (አድማ) ሳይቀበል ተከሳሾቹ በየግል ወይም በጋራ የፈፀሙትን ወንጀል ብቻ በመቁጠር ብይን ሰጥቷል፡፡ በሀገራችን የወንጀል ህግ መሰረት “ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ ሰዎች አንድ ወንጀልን ለማድረግ የተስማሙ እንደሆነ፤ ስለ ወንጀል ተካፋይነት እና ቅጣትን ስለማክበድ የተፃፉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆኑባቸዋል፡፡” ይላል፡፡ ይህም ማለት በወንጀል ተካፋይነት ማለትም አነሳሽ፣ አባሪ ወይም ወና

ወንጀል አድራጊ እንደሚባለው አድመኛ የሚለውም ተካፋይነት ደረጃ አለ ማለት ነው፡፡ አነሳሽ እራሱ ወንጀል ሳይፈፅም ሌሎች እንዲፈፅሙ ካረገ ተጠያቂ የሚሆን ሲሆን፣ የአባሪ ወንጀል ተሳታፊ ደግሞ እራሱ ወንጀል መፈፀም ውስጥ ሳይሳተፍ በማንኛውም አይነት እገዛ ምክር ወይም ቁሳዊ እርዳታ ሌሎች ወንጀል እንዲፈፅሙ ከረዳ ተጠያቂ የሚሆንበት ነው፡፡ በተመሳሳይ የአድማ ተሳታፊም በዚሁ አንቀፅ መሰረት ወንጀል ለመፈፀም የተስማማን በሙሉ የወንጀሉ ተካፋይ አድርጎ የሚቆጥር ነው፡፡ ይህ በሌሎ ሀገራት የህግ ስርአትም ያለ የተካፋይነት ደረጃ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡

ከአድማ ጋር ተያይዞ ፍርድ ቤቱ ከቀረቡለት ተከሳሾች መሀል ለምሳሌ ነገደ ጎበዜ ከሌሎች ተከሳሾች ጋር በአድማ ከተከሰሰበት ህገ መንግስቱንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ለማፍረስ መሞከር ወንጀል በወል የወንጀል አድማ አላማ ስምምነት እንዳለው የሚያሳይ በማስረጃነት የቀረበበት በግልፅ የፃፈው ይገኛል፡፡ በመፀሀፉ እንዳሰፈረው "ህገመንግስታዊ ስርአቱን መቀየር ጉዳይ አገራዊ አጀንዳ ነው፡፡" (ገፅ 11-13) "ይህ ህገ መንግስት የኢህአዴግ ድርጅታዊ ፕሮግራም እንጂ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሊያከብሩና ሊገዙለት የሚገባቸው ሰነድ ባለመሆኑ"፡፡ (ገፅ 142-143) "lzþሀ ነው ዛሬ እኛም የሀገራችን ዴሞክራቶ□በሙለጽ በተ፡ዋሚ ጎራ ተሰልፈ,ያለሀጽ የሚል ማንኛውም ድርጅት ለመፈረጅ ይህንን አደገኛ ህገጠመንግስት ከነ አደገኛ ፍልስፍናው ለመቀየር በሚደረገው ትግል በሀቅ መሳተፍ አለመሳተፉን እንደ ሀጽነኛ መስፈርት አድርገን መውሰድ ያለብንቃቃቃ (ገፅ 164) ፍርድ ቤቱ ግን የተከሳሹን ይህን ግልፅ የሀሳብ ስምምነት እየተመለከተ የተከሰሰበትን አንቀፅ በመቀየር በዝቅተኛ ቅጣት ሊያስቀጣ በሚችል ወንጀል ሊጠየቅ እንደሚችል አድርጎ ነው የበየነው፡፡

ሌላው ምሳሌ ተከሳሽ ስለሺ አንዳርጌ የቅንጅቱ አባልና ከተከሳሾቹ ጋር የጋራ የወንጀል አላማ በመያዝ በፍርድ ቤቱ ያስጠይቃሉ የተባሉ የድርጅቱን ጋዜጣዊ መግለጫዎች በማንበብና ጥሪውን በማስተላለፍ በተግባሩ የመግለጫውና የጥሪ አካል እራሱን አድርጎ ሳለ ፍርድ ቤቱ ግን በብይኑ ተከሳሹ ከማንበብ ውጪ ተሳትፎ የለውም በሊል በነፃ ለቆታል፡፡ ተከሳሹ እንደሌሎቹ የግድ ውሳኔ ሰጪነት ውስጥ

መሳተፍ ሳይጠበቅበት ይህንኑ የሚያስወነጅል መግለጫ በማሰራጨት ተሳትፎ ድርጊቱን የራሱ አድርጎ መቀበሉ እየተመለከተ በነፃ ለቆታል፡፡

ሌላው ምሳሌ ተከሳሽ ካሳሁን ከበደ በኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የአዲስ አበባ መምህራን ማህበር ስራ አስፈፃሚ ሆኖ ሳለ በኢትዮጵያ መምህራን ማህበርም ሆነ በአዲስ አበባ መምህራን ማህበር የወጡ መግለጫዎችና ቃለጉባኤዎች ቀርበውበት እያለ ፍርድ ቤቱ በነፃ ለቆታል፡፡ ለመለቀቁ መሰረት የሆነው የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ስራ አስፈፃሚ አባል ስለመሆኑ አልተረጋገጠም የሚል ነው፡፡ ይህ ግን በክሱ ከቀረበው የአድማ ትስሰር አንፃር ተገቢ አይደለም፡፡ ተከሳሹ በአዲስ አበባ መምህራን ማህበር በወጡ መግለጫዎችም ሆነ እራሱ በሰበሰባቸው ስብሰባ ቃለጉባኤዎች አመፅን የሚቀሰቅሱና የሚያወድሱ፣ ከምርጫው ጋር ተያይዞ የስራና የትራንስፖርት ማቆምን አድማ እንዲደረግ በስብሰባ በመወያየት የወል የወንጀል አላማው መፈፀም ስምምነት ያለው መሆኑን ፍርድ ቤቱ መረዳት ሲችል በአባልነት ጥያቄ በነፃ ለቆታል፡፡

የትጥቅ አመፅ የማነሳሳት የመምራትና የማደራጀት ክስን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ አምስት ተከሳሾች ብቻ እንዲከላከሉ ብየን ሰጥቷል፡፡ ይህ የወል ወንጀል አድማ ትስስርንና ተሳትፎን በሚገባ ያላገናዘበ የብይኑ ክፍል ነው፡፡ በዐቃቢ ህግ ማስረጃ መሰረት ፍርድ ቤቱ የትጥቅ አመፅ ለማንሳትና ለማደራጀታቸው ተረጋግጠባቸዋል ያላቸው አምስት ተከሳሾች ቢሆኑም የተቀሩትም በተለይም የላእላይ ኮሚቴ አባላት ይህንኑ የመሰለ አላማ እንዳለ በሚጠቁምና በሚገባቸው መልኩ አቶ ሀይሉ ሻውል እናንተ ሌሎቹ የማያውቁት እርሳቸውና የተወሰኑት ብቻ የሚያውቁት ዝግጅት እንዳለ በስብሰባ ለስልሳ የላእላይ ኮሚቴው አባላት ማስታወቃቸው በዐቃቢ ህግ የቪድዮ ማስረጃ ቀርቦ ይገኛል፡፡ ይህ አገላለፅ ሌሎቹ ተከሳሾች በውስተ ታዋቂ አለ የተባለውን የአማራጭ በአደባባይ የማይገለፅ መንገድ ተቀብለው አልፈውታል፡፡ ይህ የሌሎቹን የአድማ ስምምነት ያሳያል፡፡ በህግም ቢሆን ስምምነት በግልፅ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ሊኖር እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡ በዚህም ጉዳይ ቀሪዎቹ ተከሳሾች ቀጥተኛ ያልሆነ ስምምነት አድርገው ሳለ ፍርድ ቤቱ ይህን በሚገባ ሳያጤን እንዲከላከሉ ብይን ያልሰጠው የሚተች ነው፡፡

ከላይ ከተነሳው የአድማ (Conspiracy) ጉዳይ ባሻገር ሌላው ዋነኛ የሚተች የፍርድ ቤቱ ብይን በሀገር ክዳት ክስ ላይ የወሰደው አቋም ነው፡፡ በፍርድ ቤቱ የአብላጫ ብይን መሰረት ተከሳሾቹ የሀገር ክዳት ክስን ሙሉ በሙሉ ሊከላከሉ አይገባም ብሏል፡፡ በዚህ ክስ የወንጀል ህጉ ይዘት

> *ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ወይም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም እንዲያስከብር በግልፅ አደራ የተጣለበት ሰው*
>
> *ለ/ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት ከሚያደርግ ሀይል ጋር ወይም ለዚሁ ሀይል ጥቅም ከሚሰራ ሰው ወይም ድርጅት ጋር በመተባበር ወይም ሚስጥራዊ ግንኙነት በማድረግ ይህው ሀይል እንዲመቸውና እንዲቀናው በማናቸውም አኳህን የረዳ እንደሆነ*

የሚል ነው፡፡

የክሱ ይዘት ተከሳሾቹ ከፍ ባለ የሀገር ክዳት የጠላት ሀገር እና በዚሁ የሚደገፍ የአርበኞች ግንባር እንዲቀናውና የውጭ ወረራ የመቋቋም ሀይል እንዲፈርስ በፈፀሙት ተግባር ክስ የተመሰረተባቸው ሲሆን፣ በማስረጃነት የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ለቅንጅት በላከው ደብዳቤ አቶ ሀይሉ ሻውል የምስጋና ምላሽ እንዲፃፍና በሚቀጥለው ስብሰባቸው እንዲነበብ የመሩበት ሰነድ፣ የአርበኞች ግንባር አባላት የነበሩና የተማረኩ ምስክሮች ቀርበው አርበኞች ግንባር በትጥቅ ትግል የሚንቀሳቀስና በኤርትራ የሚደገፍ መሆኑን፣ ከቅንጅት ጋር ይህን መንግስት ለመጣል እንደሚሰራ፣ አላማቸው አንድ እንደሆነ፣ ቅንጅት ሲያሸንፍ ሀገራቸው እንደሚገቡ፣ የቅንጅትን ቅስቀሳና ዜና እንዲከታተሉ እንደሚደረግ በመጨረሻም የቅንጅት አባላት ኤርትራ ድረስ መጥተው እንደጎበኙዋቸው፣ እንዳበረታቱዋቸውና እርዳታ እንዳደረጉላቸው ምስክርነት ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህን ማስረጃ መርምሮ በቅንጅትና በአርበኞች ግንባር መሀል ግንኙነት መኖሩን በበቂ አያስረዳም በማለት የበየነው ማስረጃዎቹን በቂ ግምት ባለመስጠቱ ነው፡፡ ምክንያቱም በሁለቱ መሀከል የደብዳቤ ግንዩነት፣ የአላማ ግንኙነት እንዳለ፣ በአርበኞች ግንባር አመራርና አባላት በኩል ይህው ግንኙነትና ትብብር እንዳለ የሚታወቅ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ በመሆኑ የፍርድ ቤቱ ብይን ይህን በበቂ ያላገናዘበ መሆኑ ስለሚታይ ነው፡፡

ሌላው በዋነኛነት ለህጋዊ ትችት ክፍት የሆነው የብይኑ አካል በዘር ማጥፋት ክስ ላይ ፍርድ ቤቱ በአብላጫ ድምፅ ተከሳሾቹ ክሱን መከላከል አያስፈልጋቸውም በማለት የወሰደው አቋም ነው፡፡

ዘር ማጥፋት ወንጀል በህጋችን መሰረት

> *"ማንም ሰው በሰላምም ሆነ በጦረነት ጊዜ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጎሳ፣ በዘር፣ በዜግነት፣ በቀለም፣ በሀይማኖት ወይም በፖለቲካ አንድ የሆነን ቡድን በመላ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሰብ የጥፋቱን ድርጊት በማደራጀት ትእዛዝ በመስጠት ወይም ድርጊቱን በመፈፀም ሀ/ በማናቸውም ሁኔታ የማህበረሰሰቡን አባሎች የገደለ፣ አካላዊ ወይም ህሊናዊ ጤንነት የጎዳ፣ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ፣ ወይም ያጠፋ እንደሆነ ..." የሚል ነው፡፡*

የፍረድ ቤቱ አብላጫ አቋም በዐቃቢ ህግ ማስረጃዎች በአንዳንድ የትግሬ ብሔረሰብ አባላት አካልና ንብረት ላይ ጉዳት መፈፀሙን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ቢቀርቡም እነዚህ የዘር ማጥፋት ወንጀል ለማቋቋም የሚጠየቀውን ሀሳብ መኖር አይገልፁም፣ ይልቁንም በዐቃቢ ህግ ማስረጃ የተረጋገጡት ህገ መንግስቱንና ህገ መንግስታዊ ስርአቱን የማፍረስ ሙከራው ድርጊቶች አካል ናቸው የሚል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአቶ በድሩ አደም የተደረገው ንግግር "ወደ መጡበት እንመልሳቸዋለን፣ በኢትዮጵያ የመንግስት ስልጣን በትግሬ ብሔረሰብ ብቻ የተያዘ ነው" የሚሉት ከጥላቻ ቅስቀሳ ውጪ ዘር ማጥፋት ወንጀል ማቋቋሚያ የሆነውን የሀሳብ ክፍል (mental element) አያስረዳም ብሏል፡፡

እዚህ ላይ ፍርድ ቤቱ በሚገባ ያልተገነዘበው ጉዳይ የዘር ማጥፋት በዘር፣ በቃታ፣ በቀለም፣ በዜግነት፣ በፖለቲካ መሰረት አድርጎ ለጥቃት የማጋለጥ ድርጊትን ያካተተ መሆኑን ነው፡፡ በዐቃቢ ህግ በቀረበው ማስረጃ የኢህአዴግ አባላትና የትግራይ ብሔረሰብ አባላት ላይ በዚሁ መመዘኛ መነሻነት ፍርድ ቤቱ ከዚህ ቀደም ባሉ ክሶች የተረጋገጠው ጉዳይ በተከሳሾቹ በተቀሰቀሰው አመፅ የትግራይ ብሔረሰብ

አባላትና በኢህአዴግ አባላት ላይ ያነጣጠረ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሙከራ መደረጉ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ ግን ተከሳሾቹ ያሰራጩት የማግለል መግለጫ እና በተከሳሾቹ ቀስቃሽነት በትግራይ ብሔረሰብ አባላት አካልና ንብረት ላይ የደረሱት ጥቃቶችን የሚያረጋግጡ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ህገ መንግስታዊ ስርአቱን ከማፍረስ ሙከራ ድርጊት ከሚያስረዱ ማስረጃዎች ውስጥ የሚካተቱ እንጂ ዘር ማጥትን ለማስረዳት ብቃት ያለቸውም የሚል ብይን ሰጥቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፖለቲካን መሰረት አድርገው ከፍተኛ የቅነጅት አመራር የነበሩ በቅንጅቱ የተለያዩ የስብሰባ መድረኮች ቅንጅቱን በመወከል የቀሰቀሱት ፖለቲካን መሰረት አድርገው የገዢው ፓርቲ አባላትን ወደመጡበት እንመልሳቸዋለን በማለት ለህገወጥ ጥቃት እዲዳረጉ ማድረጋቸው በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ፤ በአንድ ብሔር ላይ በማነጣጠር "ገዢው ሁሉ ትግሬ ነው፣ የሚናቅ ትግሬ የለም፣ አማራ ኦሮሞ ሌላውም ብሔር ምንም ስልጣን የለውም በማለት በትግሬ ብሔር ላይ ያነጣጠረ ለአደጋ እንዲጋለጡ ደጋፊዎቻቸውን ሲቀሰቅሱ እንደነበር በማስረጃ ተረጋግጦ ሳለ፣ ፍርድ ቤቱ እነዚህን ማስረጃ ሁሉ በመተው የዘር ማጥፋት ሙከራ ወንጀል በበቂ ማስረጃዎች አልተረጋገጠም ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡ ከሁሉም በላይም ተኀዎችና ምስክሮች ብሔርን እና ፖለቲካ አቋማቸውን መሰረት አድርጎ ለከፍተኛ የአካልና የስነ ልቦና ጉዳት መጋለጣቸው በማስረጃ እየተረጋገጠ ይህ ህገ መንግስቱን በማፍረስ ሀሳብ የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት እንጂ የዘር ማጥፋት ሙከራ ወንጀል ድርጊት አይደለም ማለቱ ተገቢ አይደለም፡፡